# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲዊ)
# የምዕራብ ካናዳ አካል መግለጫ

መስከረም 3 ፣ 2012

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) የምዕራብ ካናዳ አካል ከመስከረም 1-3፤ 2012 ከተለያዩ ከተሞች በመጡ አባላቱ ተሳታፊነት ዓመታዊ ስብሰባውን በተሳካ ሁኔታ አካሂዷል። የስብሰባው ተሳታፊዎች ድርጅቱ ባለፈው አርባ ዓመት ባካሄደው ትግል ወቅት የተሰዉትን አባላቱን በመዘክርና አሁንም እየታገሉ ያሉትን አባላቱን በማድነቅ ዴሞክራሲያዊ ወገኖችን በማስተባበር ትግሉን ከግብ ለማድረስ ለወሳኙ ትግል ቃል ኪዳን የገቡበት ስብሰባ እንደነበረ ሲገልጽ በታላቅ ደስታ ነው።

በዚህ የምዕራብ ካናዳ የኢሕአፓ(ዴሞክራሲያዊ) ስብሰባ ላይ አገራችንና ሕዝቦቿ ያሳለፉት የስቃይና የሰቆቃ ዓመታት መራዘም በእጅጉ የሚያሳስበው ጉዳይ ነው። ስለዚህም ይህንን ለስቃዩ መራዘም ምክንያት የሆነውን የተናጠል ትግል ወደ ኅብረት ትግል ለማሳደግ ፓርቲያችን እስከዛሬ ሲያደርግ እንደነበረው ሁሉ ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶችና ስብስቦች ጋር በአንድነት ትግሉን ለማቀናጀት ያደረገውን ጥረት እናደንቃለን። በመሆኑም በትብብር ለመሥራት ቆርጠው ለሚሠሩ ኃይሎች ሁሉ የምዕራብ ካናዳ የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አባላት ያልተቆጠበ ድጋፍ ይሰጣሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፍትኀ፤ ለዴሞክራሲ፤ ለሰብዓዊ መብቶች፤ ለእኩልነትና ለነፃነት የሚበቃው በኅብረት በመታገል መሆኑን በማመን በሸንጎ መሥራችነትና በአባልነት ለተሳተፉ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች እንዲሁም አገር ወዳድ ታዋቂ ኢትዮጵያውያን ስብሰባው ከፍተኛ አድናቆቱን እየገለጸ ከጎናቸው እንደሚቆም ያረጋግጣል።

ስብሰባው በርካታ ድርጅታዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ውይይት በማድረግና ያለፉትን የትግል ሂደቶች በሚገባ ከመረመረ በኋላ በሚከተሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን አስተላልፏል።

- በተለያየ ወቅት የአምባገነኑን አገዛዝ ሥልጣን ለማስጠበቅ በወጡ የገዥው መንግሥት አፋኝ ህጎች እየተወነጀሉ በወህኒ የተወረወሩ ንፁሀን ዜጎች፤ ጋዜጠኞች፤ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላትና የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች እንዲሁም የሃይማኖት መሪዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ፤ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በጋራ ማንኛውንም የፖለቲካና የዲፕሎማሲያዊ ግፊት እንዲያደርጉ፤

- መሬት ለአራሹ በማለት የተዋደቅንለት ዓላማ አሁንም ምላሽ ካላመግኘቱም በላይ ወገኖቻችን የሚያርሱትን መሬቱ ተነጥቀው ለአካባቢ ጥበቃ ደንታ በማይሰጥ መልክ ለውጭ ሀብታሞች መሰጠቱን አጥብቀን እየተቃወመን በሕዝባችን ላይ እየተፈፀመ ያለውን በደል በያለንበት በመቃወም ዓለማቀፋዊ ትግል እንዲደረግ ጥሪ እናቀርባለን።

- በከተማ ነዋሪዎች ላይ በስመ ኢንቬስትመንት እየተፈፀመ ያለው የመሬት ዘረፋ በአስቸኳይ እንዲቆምና የዜጎች የመሬት ባለቤትነት መብት እንዲከበር፤

- የገዢው ቡድን በሃይማኖት የውስጥ ጉዳይ ማለትም በአድባራትና ገዳማት እንዲሁም በእስልምና ሃይማኖት የውስጥ ጉዳይ የሚያደርገውን ጣልቃገብነት እያወገዝን የታሰሩት የእምነቱ ተከታይ አባላት በአስቸኳይ እንዲፈቱ፤

- በአምባገነኑ መሪ ሞት ምክንያት የገዥው ቡድን ያለበትን የውሰጥ ባዶነት ለአለፉት በርካታ  በለቅሶ ውጡ ስም ሲያካሂደው የነበረው ተውኔት እጅግ አስገራሚ መሆኑን በመገንዘብ ድራማው ገዢው ቡድን ኃይሉን በማሰባሰብ በሕዝብ የተጠላውን የአገዛዙን ሥርዓት ለማስቀጠል የተሰራ ሥራ በመሆኑ ይህንን አስከፊ አገዛዝ በመጣል ሕዝባዊ ሥርዓት እንዲመሠረት የተጠናከር ትግል እንዲደረግ ጥሪ እያቀረብን የምዕራብ ካናዳ የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አባላት የድርሻቸውን ለማበርከት ዝግጁነታቸውን ያረጋግጣሉ።

- በሙስና የተዘፈቁት ህወሓት/የኢህአዴግ ሹማምንት የሀገራችንን አንጡራ ሀብትና ንብረት እየዘረፉ ወደ ውጭ ሀገር እያሸሹ የሚፈጽሙትን ሀገራዊ በደል እያወገዝን እስካሁን የተዘረፈው የሀገር ሀብት በአስቸኳይ እንዲመልሱና በውጭ የሚኖሩ ተባባሪዎቻቸውም ከዚህ እኩይ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ አጥብቀን እናስጠነቅቃለን።

- የመከላከያ ሠራዊት አባላት የሀገር ደህንነት ለማስከበር እንጂ የገዥውን ቡድን ጥቅም ለማስጠበቅ የቆመ ኃይል አለመሆኑን በመረዳት ከሕዝብ ጎን እንዲቆም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

በመጨረሻም የተባበረ የሕዝብ ትግል ብቻ ሀገራችንን ነፃ እንደሚያወጣን ተረድተን የሕዝብ ወገን ሁሉ የጋራ ትግል በማድረግ አገራችንና ሕዝባችንን የነፃነት፤ የሰላምና ብልፅግና ባለቤት ለማድረግ ለዚህ ታላቅ መስዋዕትነት የፆታ፤ የሃይማኖት፤ የዕድሜ፤ የአካባቢ፤ የፖለቲካ ልዩነትን አቻችለን በጋራ እነድንነሳ ስብሰባችን ጥሪውን ያቀርባል።

ኢትዮጵያ በልጆቿ የተባበረ ክንድ በነፃነት ለዘላለም ትኖራለች!